# የስኬታማ ጥረታችን ሃውልት - ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ

አዲስ ቶልቻ 03/17/14

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በይፋ ከተጀመረ ሦስት አመት ሊሞላው ቀናት ቀርተውታል። የግድቡ የመሰረተ ድንጋይ በታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ የተጣለው መጋቢት 24፣ 2004 ዓ/ም ነበር። ይህ መለስ ዜናዊን "ሳይደፈር የኖረውን የደፈረ መሪ" ያሰኘ ተግባር ትልቅ ሃገራዊ መግባባት ተፈጥሮበታል። በቅርብ ጊዜ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የዚህ አይነት ታላቅ ሃገራዊ መግባባት የታየው በኤርትራ መንግስት ወረራ ተፈፅሞብን የነበረ ጊዜ መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ።

በአባይ ወንዝ ላይ የሚገነባው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ላይ የታየው አገራዊ መግባባት በቀዳሚነት የመነጨው ህዝቡ የተፈጥሮ ሃብቱን ተጠቅሞ ከድህነት ለመውጣት ካለው ፅኑ ፍላጎት ነው። ግብፅ፣ ኢትዮጵያ የአባይን ውሃ የመጠቀም መብት እንደሌላት አድርጋ ስታስወራ ስለኖረች ለአገራዊ መግባባቱ የተለየ ገፅታ ሰጥቶት ሊሆን መቻሉ ግን እውነት ነው። ይህ ሁኔታ ቁጭት ፈጥሮ ቆይቷልና።

መንግስታትና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ከዚህ የግብፅ አቋም በመነሳት ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ ለምታከናውነው ማንኛውም ልማት፣ እንኳን እርዳታ ብድር ለመስጠት ፍቃደኛ ሳይሆኑ መቆየታቸው ይታወቃል። እዚህ ላይ ሁኔታውን በግልፅ ለማሳየት አንድ ታሪክ ላስታውሳችሁ፡፡

ከሃያ አምስት ዓመት በፊት የፊንጫ የስኳር ፋብሪካን ለመገንባት የዓለም ባንክ ብድር ተጠይቆ ነበር፡፡ የፊንጫ ወንዝ የአባይ ገባር በመሆኑ ባንኩ የፕሮጀክቱን ክንውን ግብፅ ሳትፈቅድ ብድር እንደማይሰጥ ያሳውቃል፡፡ በኋላ ባንኩ ጥያቄውን ለግብፅ አቅርቦ ምልስ ሳትሰጥ ስድስት ወር ትቆያለች፡፡ ከስድስት ወር በኋላ መልስ አለመስጠቷ እንደመስማማት ተቆጥሮ ብድሩ ተፈቀደ፡፡ ልብ በሉ፣ የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚጠቀመው ወደግብፅ ከሚፈሰው የአባይ ውሃ ከ1 ከመቶ በታች ነው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን በራሱ አቅም አስገንበቶ የታቸኞቹ ተፋሰስ ሃገራት በተለይ የግብፅ አካሄድ የፈጠረበትን የዘመናት ቁጭቱን ለመወጣት የነበረው ስሜት የተፈጥሮ ሃብቱን ተጠቅሞ ከድህነት ለመውጣት ያለው ፍላጎት የፈጠረውን ሃገራዊ መግባባት የበለጠ አጠናክሮታል።

ሁላችንም እንደምናስታውሰው የግድቡን የመሰረት ድንጋይ መጣል ተከትሎ በመላው አገሪቱ የሚኖሩ ብሄሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ግድቡን በራስ አቅም ለማስገንባት ከዳር እስከዳር አደባባይ ወጥተው ቃል ገብተው ነበር። ይህ ሕዝባዊ ማዕበል ምን ያህል ጠንካራ ሃገራዊ መግባባት እንደተፈጠረ በገሃድ አሳይቷል።

እዚህ ላይ የህዳሴውን ግድብ የመሰረት ድንጋይ መጣል ተከትሎ ግንቦት 20፣ 2003 ዓ/ም በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ በሚሊየን የሚቆጠሩ የከተማዋ ነዋሪዎች ለሕዳሴው ግድብ ያላቸውን ድጋፍ ለመግለፅ በወጡበት ወቅት የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መስራች አባት ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ ባደረጉት አጭር ታሪካዊ ንግግር የግድቡ መገንባት ላይ የተፈጠረውን ሃገራዊ መግባባት ምንጭ አገሪቱ ከጀመረችው የህዳሴው ጉዞ ጋር አገናኝተው ውብና ግልፅ በሆነ አኳኋን አስቀምጠውታል። እናም የግድቡ ግንባታ የተጀመረበትን ሦስተኛ ዓመት ለመዘከር በተቃረብንበት ወቅት ይህን ንግግር ለሕዝቡ ማስታወስ አስፈላጊ ሆኖ ስለተሰማኝ ቀንጭቤ ማቅረብ ወድጃለሁ። የመለስ ዜናዊ ንግግር፤

*. . . ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ኢትዮጵያውያን የውጭ እርዳታና ብድር ካላገኙ በቀር በአባይ ተፋሰስ ላይ ምንም ነገር መስራት አይችሉም ተብለን የተፈረጅንበትን የድህነትና የአቅመቢስነት ታሪክ የሰበረ ግድብ ነው፡፡*

*የውጭ እርዳታና ብድር እንዳናገኝ በማድረግ የተፈጥሮ ሃብታችንን እንዳንጠቀም አድርገው የነበሩ ኃይሎችን በቁም በቀል መልክ ሳንመለከት፣ በጋራ እንጠቀም በማለት አርቆ አስተዋይነታችንን ለዓለም ግልጥልጥ አድርጎ ያሳየ ግድብ ነው። ትክክለኛ የልማት አቅጣጫ እስከያዝን ድረስ ቁርስና ራታችንን በመተው ጭምር በድህነት ላይ ከመዝመት ወደኋላ እንደማንል ያስመሰከረ ግድብ ነው።*

እናም ታላቁ የህዳሴ ግድብ ለእኛ ታላቅ የኤሌክተሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ብቻ አይደለም። ብዝሃነታችንን በእግባቡ የሚያስተናግድ የፖለቲካ ስርአት ገንብተን፣ ትክክለኛ የልማት አቅጣጫ ቀይሰን፣ ከነበርንበት የድህነት አረንቋ ተላቀን ቀደምት ኢትዮጵያውያን ወደነበሩበት የዓለም የሥልጣኔ ጠርዝ ላይ ለመድረስ ለረጅሙ የህዳሴ ጉዞ መነሳታችንን የሚያሳይ የቁርጠኝነታችን ሃውልት ነው።

በጀመርነው የህዳሴ ጉዞ አበረታች ውጤት ማግኘታችንን የሚያሳይ፣ ከእንግዲህ በአባይ ተፋሰስ ላይ ባለቤትና ተጠቃሚ እንጂ የበይ ተመልካች እንደማንሆን፣ በተፈጥሮ ሃብታችን በአግባቡ እንዳንጠቀም የሚከለክለን ኃይል እንደማይኖር የሚያረጋግጥ የስኬታማ ጥረታችን ሃውልት ነው።

**በሚሊየን የሚቆጠሩ ዜጎች በገንዘባቸው፣ በንብረታቸው፣ በእውቀታቸው የሚገነቡት የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የላብ ፊርማ ያረፈበት ግድብ በመሆኑ፣ የህዳሴው ጉዛችን መሃንዲሶች እኛው፣ ግንበኞችና ሰራተኞች እኛው፣ የፋይናንስ ምንጭና አስተባባሪዎች እኛው በአጠቃላይ የህዳሴ ግዟችን ባለቤቶች እኛው መሆናችንን የሚያሳይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታችን ነው።**

የህዳሴ ግድብ ጉዳይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዳርዳር ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ያነቃነቀውና የመንፈስ ኩራት እንዲያድርበት ያደረገው፣ ከግድብነት አልፎ ድህነትንና ከድህነት የሚመነጨውን ውርደት ታሪክ ለማደረገ ስኬታማ ጉዞ መጀመራችንን የሚያረጋግጥለት ተጨባጭ ግዙፍ ፕሮጀክት በመሆኑ ነው።

የኢትዮጵያ መንግስትና ድርጅታችን ኢህአዴግ እንደሌላው ዜጋ ሁሉ በዚህ ታላቅ ግድብ ግንባታና በዙሪያው በተፈጠረው ሕዝባዊ ማእበል በእጅጉ ይኮራሉ። በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ መንግስትና ድርጅታችን ኢህአዴግ የህዳሴ ግድቡን ከዳር ለማደረስ፣ ይልቁንም በእቅድ ከተያዘው ግዜና ወጪ ባነሰ መንገድ ለመስራት ላንዳፍታም ሳያመነቱ ሌት ተቀን እንደሚረባረቡ፣ የህዝቡን ልማታዊ መነሳሳት በአግባቡ አደራጅተው እንደሚንቀሳቀሱ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።

*የህዳሴው ግድብ የአጠቃላይ የልማት ርብርባችን ተምሳሌት እንጂ የልማት ስራችን መጀመሪያና መጨረሻ ባለመሆኑ፣ የግድቡ ሥራ ሌሎች ታላላቅ የልማት ሥራዎቻችንን በማያስተጓጉል መልኩ እንደሚፈፀም ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።*

*መጪው ጉዞ የህዳሴ ጉዞ ስለሆነ ብሩህ ነው። ለልማት ቆርጦ የተነሳው ሕዝባችን የሚሳነው ነገር የለም። ድህነትና ውረደትን ያለአንዳች ጥርጥር ታሪክ እናደርጋለን።* የሚል ነበር።

የኢትዮጵያ ህዝብ አደባባይ ወጥቶ ለህዳሴው ግድብ ግንባታ ያለውን ድጋፍ በመግለፅና ግድቡን በራስ አቅም ለማሰገንባት ቃል በመግባት ብቻ አልተገደበም። ይህን በተግባር አረጋግጧል። ለግድቡ ግንባታ የአቅሙን ያህል ድጋፍ ለማድረግ ቃል በገባው መሰረት ተግባራዊ ማድረግ ጀም…ል። የመንግስት ሰራተኞች አብዛኞቹ በዓመት የወር ደሞዛቸውን ለግድቡ ግንባታ ለመለገስ ቃል የገቡት ግንባታው በተበሰረ ማግስት ነበር።

ከመንግስት ሰራተኞች ጋር የግል ድርጅቶች ሰራተኞችም በተመሳሳይ ሁኔታ የወር ደሞዛቸውን ለመለገስ ያላቸውን ፍቃድ በይፋ አሳውቀው ተግባራዊ ማድረግ የጀመሩት የግደቡን ግንባታ መበሰር ተከትሎ ነበር። መንግስት ይህን በልገሳ ሊሰጥ የነበረውን ገንዘብ ከ5 አመት በኋላ ከወለድ ክፍያ ጋር ወደሚመለስ የቁጠባ ቦንድ ግዢ እንዲቀየር አደረገ።

የተቀረውም የህብረተሰብ ክፍል፣ ለዕለት ጉርሳቸው ከሚሰሩ እንጨትና ቅጠል ቸርቻሪ ዜጎች ጀምሮ እስከ ቢሊየነር ባለፀጎች ግድቡን በዜጎች አቅም ለመደገፍ ቃል ገብተው ነበር። በልገሳ ገንዘብ መስጠት የሚቻል መሆኑ ሳይዘጋ፣ መንግስት የቁጠባ ቦንድ ግዢ አማራጭንም በማቅረቡ፣ የነጋዴው የህብረተሰብ ክፍል በቢሊዮን በሚቆጠር ገንዘብ የህዳሴውን ግድብ ቦንድ ለመግዛት ቃል ገባ።

የግድቡን ግንባታ ለማደናቀፍ የሚሹ የኢትዮጵያ ጠላቶች ተላላኪ ቅጥረኞች እንደፈለጉ በሚፈነጩባቸው ሰሜን አሜሪካና የአውሮፓ አገራትም፣ የቅጥረኞቹን የማሸማቀቅ ዘመቻ ከምንም ያልቆጠሩ በርካታ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለግድቡ ግንባታ የቦንድ ግዢና የገንዘብ ልገሳ አድርገዋል። በዚህ የህዝብ ተሳትፎ እስካሁን የ7 ነጥብ 1 ቢሊየን ብር የቦንድ ግዢ ተፈፅሟል፡፡

የቁጠባ ቦንድ ግዥው "በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ" እንዲሉ የግድቡን ግንባታ ከመደገፍ ጎን ለጎን ቁጠባንም አበረታቷል። ከቁጠባ ቦንድ ግዥው በኋላ በኢትዮጵያ የነበረው አገራዊ ቁጠባ ከ5 በመቶ ወደ 17 ነጥብ 7 በመቶ ማደግ ችሏል፡፡

ባለፉት ሶስት አመታት በኢትዮጵያውያንና በትውልደ ኢትዮጵያውያን አንጡራ ሃብት በመገንባት ላይ ያለው ግድብ ግንባታ ስራ ከ30 በመቶ በላይ ተከናውኗል። ለዚህ ግንባታ 27 ቢሊየን ብር ወጪ ተደርጓል። ይህ ወጪ 26 በመቶ ማለትም 7 ነጥብ 1 ቢሊየን ብር በህዝብ የተሸፈነ ነው፡፡ የህዝቡ ተሳትፎ ከታቀደው በላይ መሆኑም ተገልጿል።

ግድቡን የማስገንባቱ ኃላፊነት ከኢትዮጵያ ህዝብ የተረከበው የኢፌዴሪ መንግስት የግድቡን ግንባታ ለሰኮንድ እንኳን ሳይቋረጥ ለፍፃሜ እንደሚበቃ ገልፆ እንደነበረ ይታወሳል። ይህንኑ አቋሙን በተግባር አረጋግጧል፣ ለወደፊትም ተግባራዊ እንደሚያደርግ በተደጋጋሚ ሲገልፅ ቆይቷል።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ሃብት ቢሆንም፣ እያንዳንዱ ዜጋ የራሱ ንብረት ለሆነው ግድብ ድርሻውን ያበረከተ ቢሆንም፣ ኢትዮጵያውያን ለራሳቸው ያደረጉት ይህ ተግባር ለቀጣይ ትውልዶች እንዳደረጉት የሚቆጠር ነው። በመሆኑም አንዳችን ሌላችንን ለናመሰግን፤ ልንመሰጋገን ይገባል።

እስካሁን ላለው እየተመሰጋገንን፣ ቀሪው የግድቡ ስራም እኛንና እኛን ብቻ የሚጠብቅ መሆኑን አስታውሰን የጀመርነውን ለማስጨረስ ቀበቷቻችንን/ መቀነታችንን ጠበቅ ማድረግ ይኖርብናል። የኢትዮጵያ ህዝብ በግድቡ ላይ

የጣለውን ተስፋ፣ በራሱ አቅም ለማስገንባት ቃል በገባው መሰረት የጀመረውን በመፈፀም ዕውን ማድረግ አለበት፤ የጀመረነውን መጨረስ አለብን።

እንግዲህ ግድቡን የማስገንባት አቅም በኢትዮጵያውያን እጅ ብቻ ያለ በመሆኑ ይህን ለማድረግ የማንንም ፍቃድ አንጠይቅም። በራሳችን እጅ ያለ በመሆኑ ማንም በተቃራኒው እንድንወስን ሊያደርገን አይችልም። ይሁን እንጂ ከዚህ ቀደም “የአባይ ውሃ ብቸኛ ባለቤት ነኝ፣ በብቸኝነት የመጠቀም መብት አለኝ” ስትል የኖረችው ግብፅ የግድቡን ግንባታ ለማደናቀፍ እየተራወጠች ነው።

ኢትዮጵያ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ግንባታ ያስጀመረችው በዓለም አቀፍ ህጎችና የናይል ተፋሰስ አገራት ከአራት ዓመት በፊት የተፈራረሙበትን የናይል አጠቃቀም የስምምነት ማዕቀፍ መሰረት በማድረግ ነው። በመሆኑም በግብፅ ላይ ጉልህ ጉዳት የሚያስከትል አንዳችም እርምጃ አልወሰደችም፤ ይህን የማድረግ ፍላጎትም የላትም። የግድቡ ግንባታ እንዲያውም የታችኞቹ የተፋሰስ ሃገራት ለሆኑት ሱዳንና ግብፅ ጥቅሞች ይኖሩታል። ኢትዮጵያ የግድቡ የመሰረ ድንጋይ ከተጣለ ግዜ ጀምሮ ይህን ስትገልፅ ቆይታለች።

ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ የህዳሴውን ግድብ የመሰረት ድንጋይ በጣሉበት ስንስርአት ላይ ባደረጉት ንግግር ይህን እውነታ እንደሚከተለው ገልፀውት ነበር፡፡

*. . . የዚህ ታላቅ ፕሮጀክት ጥቅም በኢትዮጵያ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ሁሉንም ጎረቤቶቻችንን በተለይም የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት የሆኑትን ሱዳንና ግብፅን በእጅጉ የሚጠቅም ነው። ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ወንዙ ተሸክሞት ይሄድ የነበረው ደለል ስለሚቀር፣ በግብፅና ሱዳን ያሉ ግድቦች፣ በተለይም በደለል እየሞላ የሚሰጠውን ጥቅም በጣም በከፍተኛ መጠን የቀነሰው የሮሰሪስ ግድብ ከዚህ ነፃ ይሆናል።*

*ለዘመናት በአባይ ውሃ ሙላት ይጥለቀለቁ የነበሩ አካባቢዎች፣ በተለይም የሱዳን አካባቢዎች ይህ ግድብ ሲጠናቀቅ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ከአደጋው ነፃ*

የሆናሉ። ከግድቡ የሚመነጨው ኃይል ከራሳችንም አልፎ ለጎረቤታችን ሃገሮች በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ ስለሆነ፣ ግብፅና ሱዳን ከዚህ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

ግድቡ በሱዳንና ግብፅ በሚያልፈው የወንዙ ክልልና ግድቦች ዙሪያ የሚታየውን ከፍተኛ የውሃ ትነት ቀንሶ፣ ዓመቱን ሙሉ የተስተካከለ የውሃ ፍሰት እንዲኖር ስለሚያደርግ፣ በወንዙ ተጋሪ ሃገራት መሃከል በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ የሚታዩ ልዩነቶችን የሁሉንም ሃገራት ጥቅም በሚያስጠብቅ አኳኋን ለመፍታት ያስችላል።

ይህ የግድቡ የመሰረት ድንጋይ ሲቀመጥ በመለስ ዜናዊ የተገለፀ ሃሳብ ከጅምሩም ሱዳንና ግብፅን የመጉዳት ዓላማ እንዳልነበረው በግልፅ ያሳያል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ የነፃነት ታሪክ ውስጥ ፣ በአፍሪካ ወንድማማችነት- ፓን አፍሪካንዚም ውስጥ ያሉት ድርሻ፣ ከአጎራባች ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት፣ በአጠቃላይ የምትከተለው የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እንዲሁም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በምስራቅ አፍሪካ ብሎም በአፍሪካ ሰላም እንዲሰፍን እያደረገችው ያለው አስተዋፅኦ የሌሎቹ ሃገራትን ጥቅምና ፍላጎት እንደምታከብር በግልፅ ያሳያል፡፡ ከዚህ በመነሳት ኢትዮጵያ በግድቡ ግንባታ ግብፅን የመጉዳት አንዳችም የግባር እንደማታከናውን መናገር ይቻላል።

ኢትዮጵያ በግድቡ ግንባታ ግብፅን የመጉዳት ፍላጎት የሌላት መሆኑን በተግባር ለማረጋገጥ ከሶስቱ ሃገራት፤ ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብፅ እንዲሁም የዓለም አቀፍ ተቋማት ተወካዮች የተካተቱበት የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲቋቋም ፈቅዳለች። በራስዋ ድንበር ውስጥ የሚፈሰውን ውሃ የታችኞች ተፋሰስ ሃገራት ላይ የጎላ ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ የመጠቀም መብት እንዳላት ኢትዮጵያ ታውቃለች። ይህን ለማድረግ የሌሎችን ፍቃድ ማግኘት እንደማይጠበቅባትም ታውቃለች። ይሁን እንጂ ግድቡን የሚገመግም የሶስተዮሽ የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲቋቋም ፈቅዳለች። ይህ በየትኛውም አገር መቼም ተደርጎ የማያውቅ ነው።

እነዚህ ሁኔታዎች ኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ የበላይነት እንዲኖራት አድርገዋል። ግብፅ በዲፕሎማሲ ጫና አሳድራለሁ በሚል በቅርቡ የጀመረችው እንቅስቃሴ ምንም ተጨባጭ ውጤት ማሳየት ያልቻለው ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ሊሆን መቻሉ እርግጥ ነው።

በቅርቡ የግብፅ መንግስት የህዳሴውን ግድብ ለማስቆም ጉዳዩን ወደተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤትና ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንደሚወስድ ገልፆ እንደነበረ ይታወሳል። ይህ የትም እንደማይደርስ ሲገነዘብ ደግሞ በኢትዮጵያ ላይ ጫና ማሳደር ይችላሉ ወዳላቸው አገራት ፊቱን አዙሯል። እነዚህም የህዳሴውን ግድብ የሚገነባው ሳሊኒ ኩባንያ የተመሰረተበት አገር ጣሊያን፣ የአባይ ተፋሰስ አባል የሆነችው ታንዛንያና ለኢትዮጵያ የሰብአዊ እርዳታ የምታደርገው ኖርዌይ ናቸው።

እስካሁን በግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነቢል ፋህሚ የሚመራ የልኡካን ቡድን ወደጣሊያንና ታንዛኒያ ተጉዟል። የልኡካን ቡድኑ ከጉብኝቱ በኋላ "የህዳሴው ግድብ ግንባታ ላይ ተፅእኖ ማሳደር የሚያስችል ውጤት አግኝቼያለሁ" የሚል መግለጫ ሰጥቷል። ይሁን እንጂ "ተፅእኖ ሊያሳድሩ ነው" የተባሉት ሃገራት የግብፅ ባለስልጣናትን መግለጫ ተከትሎ የመንግስታቸውን አቋም ይፋ ሲያደርጉ የሰማነው እውነት ግብፅ ከገለፀችው የተለየ ሆኖ ተገኝቷል።

የግብፅ የልኡካን ቡድን ለጣልያን መንግስት ያቀረበውን ጥያቄና የመንግስታቸውን አቋም አስመልክተው በግብፅ የጣሊያን አምባሳደር በሰጡት መግለጫ "የመንግሥታቸው አቋም በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት መሞከር ብቻ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ላይ እየተሳተፈ የሚገኘው ሳሊኒ በመባል የሚታወቀው የጣሊያን ኩባንያ የግል ነው። የጣሊያን መንግሥትም በግል ኩባንያዎች አሰራር ውስጥ ጣልቃ የመባት ምንም ዓይነት ሥልጣን የለውም" ብለዋል።

በተመሳሳይ የታንዛኒያው ፕሬዚዳንት ጃካያ ኪኬዌቴ ከገበፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ናቢል ፋሚ ጋር ከተወያዩ በኋላ፣ አገራቸው ታንዛኒያ የአባይ ወንዝ የሚያልፍበት የትኛውም አገር በወንዙ የመጠቀም መብት እንዳለው ለግብፅ የልኡካን ቡድን መግለፃቸውን አስታውቀዋል። አያይዘውም “ ‘ወንዙ የሚያቋርጣቸው አገራት ውሃውን ለልማታቸው ለመጠቀም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ እኩል መብት አላቸው’ የሚለው ግልፅ የሆነው የታንዛኒያ አቋም ነው” ብለዋል። ፕሬዝዳንት ኪኬዌቴ በግላቸው ፍትሃዊ በሆነ የውሃ አጠቃቀም የሚያምኑ መሆናቸውንም አስታውቀዋል።

እናም ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ እንደገለፁት *የጀመርነው የህዳሴ ጉዞ አበረታች ውጤት ማግኘታችንን የሚያሳይ፣ ከእንግዲህ በአባይ ተፋሰስ ላይ ባለቤትና ተጠቃሚ እንጂ የበይ ተመልካች እንደማንሆን፣ በተፈጥሮ ሃብታችን በአግባቡ እንዳንጠቀም የሚከለክለን ኃይል እንደማይኖር የሚያረጋግጥ የስኬታማ ጥረታችን ሃውልት* የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በኢትዮጵያውያን እውን እየሆነ ነው።